“በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።

# የክርስቶስ ልደት የመላው ዓለም ልደት ነው።

አንድ የተባረከ ልጅ ከአንድ ቤተሰብ ቢወለድ ቤተሰቡንና ጎረቤቱን ማገልገልና መርዳት ይችላል እንጂ የሀገሩን ሰው ሁሉ ለመርዳት አይችልም። የክርስቶስ ልደት ግን ከሰዎች ልደት የተለየ ነው። ምክንያቱም ክርስቶስ የተወለደው ለአንድ ቤተሰብ ወይም ለአንድ ነገድ ሳይሆን ለሚያምንበት ለመላው ዓለም ድህነት ነው። ከሙሴ ጀምረው በየጊዜው የተነት ነቢያት የክርስቶስን ወደ ዓለም መምጣት በልዩ ልዩ ምሳሌ ገልፀው አሰተምረው ስለነበር በጨለማ እና በሞት ጥላ ውስጥ የነበረው ሕዝብ ሁሉ የልደቱን ብርሀን ለማየት ይናፍቅ ነበር።

ነገር ግን የክርስቶስ ወደ ዓለም መምጣት የሰው ልጆች መብት እንዲጠበቅ አንዱ ሌላውን እንዳያጠቃው ሰላምን በዓለም ላይ ለመመስረት እንደሆነ የተነገረው ትንቢት ያስረዳናል። ጐላ ብለው ከሚነገሩ ትንቢቶች ነቢዩ ኢሳይያስ እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ብላ ትሰይመዋለች ብሎ ተናግሯል። የመዳን ተስፋ አብስሯል።

አማኑኤል ማለት እግዚአብሔር ከኛ ጋራ ነው ማለት በመሆኑ ትንቢቱ ለሰማው ሁሉ በጣም ያስደስታል። ምክንያቱም ኢሳይያስ ትንቢቱን በተናገረበት ጊዜ ዘመኑ የችግርና የጭንቅ ዘመን ስለነበር ነው። ይኸውም አንዱ የአንዱን መብት ለመውረርና ለመደምሰስ የሚዘጋጅበት ጊዜ ሥጋዊ ጭንቀት የበዛበት ከመሆኑም በላይ ሰው በስህተቱ ከእግዚአብሔር ጋር የተጣላበት፣ ዓለም በጨለማ የተዋጠበት፣ ሞት የሰለጠነበት ስለሆነ በዚያ ጭንቅ ዘመን እግዚአብሔር ከኛ ጋራ ነው የሚል ድምፅ መስማት ታላቅ ተስፋ ነበር።

እግዚአብሔር ከኛ ጋራ ሆኖ የሚረዳው ሕዝብ ማንንም ሊፈራና ሊደነግጥ ለማንም ሊንበረከክ ማንም ሊያጠቃውና ሊደፍረው አይችልም። ኢሳይያስ አማኑኤል ማለት እግዚአብሔር ከኛ ጋራ ነው ብሎ እንደተናገረው ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም በአምላካዊ ግብር በፈቃዱ ተጸንሶ በመወለዱ በልደቱ ብርሃን ለመላው ዓለም አብርቷል። የሰላም አለቃ የብርሀን መገኛ ኢየሱስ ክርስቶስ በማኅፀነ ማርያም ሳለ ዮሴፍ እጅግ ይጨነቅና ይጠበብ ስለነበር መልዐኩ ቀደም ብሎ ኢሳይያስ የተናገረውን ትንቢት በመግለፅ ሲያስረዳ የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ ከእርሷ የተጸነሰው በመንፈስ ቅዱስ ነውና የምትጠብቃት እጮኛህን ማርያምን ለመወሰድ አትፍራ ልጅም ትወልዳለች እርሱም ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ ከእግዚአብሔር በነቢይ የተነገረው ይፈፀም ዘንድ እንሆ ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ትለዋለች ትርጓሜውም እግዚአብሔር ከእኛ ጋራ ሆነ ማለት ነው ። ማቴ፩፥፳-፳፫

ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መጥቶ የእኛን ሥጋ ለበሰ ከእኛ ጋራ ከሆነ ጀምሮ ሰዎች ሁሉ የጨለማውን ስራ አውጥተው ጥለው በእውነተኛ ብርሃን እንዲመላለሱ ከድንቁርና ወደ እውቀት ከኃጢአት ወደ ጽድቅ ከመገዛት ወደ ነፃነት ተመልሰው የብርሃን ልጆች ይሆኑ ዘንድ አወጀ። ይህም የሰላም አዋጅ ቀስ በቀስ በዓለም ሁሉ ተሰማ። ብዙዎቹም የልደቱን ብርሃን በማየታቸው ደስታቸውን ልዩ ልዩ ስጦታዎችና እጅ መንሻዎች በማቅረብ ገለፁ።

ለአባታችን ለአዳም ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሀለሁ፡ ያለው ተስፋ ደረሰ ተፈፀመ። የልደቱ ብርሃን በቤተልሔም በአበራ ጊዜ በሰው ልጆች ላይ ያለው ከባድ ቀንበር ቀለለ። የዲያብሎስ ስልጣን ተደመሰሰ።

ምድር ሁሉ እልል አለች። በጠቅላላው በሰማይና በምድር እርቅ ስለሆነ በአርአያ እግዚአብሔር የተፈጠረ ቀርቶ እንስሳትና አራዊት ግዕዛን የሌላቸው ፍጥረታት ሁሉ በልደቱ ተደስቷል። መላዕክት የልደቱን ዜና ለሠው ልጆች ደስ በሚያሰኝ አነጋገር እንሆ የዓለም መድኃኒት ክርስቶስ ተወልዶላቹሀልና ደስ ይበላችሁ። ይህንንም ለመረዳት ብትፈልጉ የተወለደው ሕጻን በቤተልሔም በበረት ተኝቶ በመጠቅለያ ተጠቅልሎ ታገኙታላችሁ ከነ ምልክቱ አስረድተዋል።

ከብቶቻችውን ይጠብቁ የነበሩ እረኞችም ተደስተው ደስታቸውን ለመግለጽ ክርስቶስ ወደ ተወለደበት በሌሊት ሲሄዱ ትንቢቱን በይበልጥ የሚያውቁት ከአልጋቸው ላይ አልተንቀሳቀሱም ነበር። ሰብዓ ሰገል ሠራዊቶቻቸውን አስከትለው ብዙ ጠቅላይ ግዛቶችንና ብዙ አገሮችን አቋርጠው በኮከብ እየተማሩ መጥተው በተወለደው አምላክ እጅ መንሻ ሲያቀርቡ ክርስቶስ በተወለደበት አካባቢ ያሉት ነገስታትና መኳንንት በተንኮልና በሽንገላ አነጋገር “እንሰግድለት ዘንድ

ቦታውን አይታችሁ ስትመለሱ ንገሩን ይሉ ነበር። ነገር ግን ከንቱ ምኞታቸውና ሀሳባቸው ራሳቸውን አጥፍቷቸዋል ።

የእግዚአብሔር መልዐክ “በዳዊት ሀገር መድኅን ክርስቶስ ተወልዶላችኃልና ብሎ እንደተናገረው የኢትዮጵያ ሊቅ ቅዱስ ያሬድ ስለክርስቶስ ልደት ብሉያትንና ሐዲሳትን እያነፃፀረ ሲናገር ዮም ተወልደ መድኃኔ ዓለም ዮም ተወልደ ከሣቴ ብርሃን መድኃኒነ ተወልደ ነዋ ይእዜኒ ለሰላም ንትልዋ፡ ዮም ተወልደ እግዚእ ወመድኅን ቤዛ ኵሎ ዓለም ። ይህም ማለት ዛሬ እውነተኛውን ብርሀን የሚያበራ የዓለም መድኃኒት ተወለደ።የዓለም ቤዛ ተወለደ ። እንሆ መድኃኔ ዓለም በመወለዱ በምድር ላይ ሰላም ነግሳለችና ሰለምን እንከተላት ፡ እርሱ በልደቱ ዓለምን ሰላምእንዳደረጋት እንወቅ የሚል ሲሆን የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያንም የመልዐኩንና የቅዱስ ያሬድን ቃል በማስተባበር፡ዮም ተወልደ መድኃኔ ዓለም ዛሬ የዓለም መድኃኒት ተወለደ። የልደቱ ብርሀን በዓለም መላ የመወለዱም ዜና የሰሙ ሁሉ እጅ መንሻ ይዘው ቀረቡ ክርስቶስ በመወለዱ ሊደሰቱ የቻሉት የሰው ልጆች ብቻ ሳይሆኑ በምድር ላይ ያሉት ትራሮችና አፍላጋት እንስሳትም ናቸው።

ይኸውም ይታወቅ ዘንድ ሀበ እንተ ልደቱ ለክርስቶስ አድባር ኮኑ ኅብስተ ሕይወት ወዕፅወኒ ወገዳምኒ ፈረዩ አስካለ በረከት፡ወማየ ባህርኒ ኮነት ሀሊበ ወመዓረ ስለ ክርስቶስ ልደት ክብር ተራሮች የሕይወት ኅብስት ሆኑ የበረሀ እንጨቶችም የበረከት ፍሬንአፈሩ፡ባህርም ወተትና መዓር ሆነች፡ እንስሳትም በዚህ ዕለት የተወለደው የሰማይና የምድር ፈጣሪመሆኑን አውቀው እስትንፋሳቸውን ገበሩ በዛሬው ዕለት ሰውና መላዕክት አን ሆነው አመሰገኑ።ከዚህ በፊት ያልታዩ መላዕክት በልዱቱ ቀን ተገልጠው አብረው ከሰው ልጆች ጋር ተደሰቱ፡የሰው ልጆች መላዕክት ተባሉ። እያሉ ይህንንና ይህን የመሳሰለውን ልደቱን የሚያነሳውን ምስጋና በዝማሬ በማኅሌት ያለማቋረጥ ሌሊቱን ሙሉ ስታመሰግን ታድራለች።

እኛስ ለዚህ ደስታ ምን አይነት አምኃ አዘጋጅተናል? የክርስቶስ ልደት በዚያን ዘመን ለነበሩ ብቻ የተሰጠ በመሆኑ ደስታው በዚያው ተፈፅሞ የቀረ አይደለም።ትውልድ ሲያልፍ ደስታው አብሮ አያልፍም።ካለው ትውልድ ጋር ይኖራል ።የክርስቶስ ልደት በአመቱ ሁልጊዜ አዲስ ልደት አዲስ አከባበር ሊሆን ስለተገባው/ስለሚገባው/ በየዓመቱ ዮም ተወለደ ቤዛ ኵሉ ዓለም ዮም ተወለደ መድኃኔ ዓለም እንላለን። የክርስቶስን የልደት በዓል ዓመቱን ሙሉ በደስታ ስለምንጠባበቀው እንደ ተወዳጅነቱ መጠን አዲስ ሆኖ እናገኘዋለን። የደስታው መዓዛ ሰውነታችንን ያድሰዋል።የልደቱ ብርሃንም ዓይነ ልቦናችንን ያበራልናል እዝነ ኅሊናችንን ይከፍትልናል።

ከላይ እንደተገለፀው ሁሉ እንሆ በዳዊት ሀገር መድኅን ክርስቶስ ተወልዷላችኋል ያለው የመልዐኩ ቃልና ቅዱስ ያሬድ ስለልደቱ ሰፋ አድርጎ የተናገረው የምስጋና ቃል በጥቂቶች ካህናት ብቻ መወሰን የለበትም።/አይገባውም/።

የድኅነት ተካፋዮች ካህናት ብቻ አይደሉም ።ምዕመናን ሁሉ ናቸው እንጂ እውነቱ ይህ ከሆነ ታላቅ የሆነ የልደት ምስጋና ክርስቲያን ለሆኑ ሁሉ ሴት ወንድ ሕፃናት ሽማግሌ ሳይል ለሁሉም የሚገባ ነው።

“ወኲሉ ፍጥረት ተፈስሐ በምፅአት ፡ከፍጥረት ሁሉ ወደዚህ ዓለም በመምጣትህ ተደሰተ ” ብሎ ኤፍሬም እንደተናገረው የልደቱ ደስታ ለእንስሳት ሳይቀር ለፍጥረታት ሁሉ እንደሆነ ያስረዳናል። ስለዚህ እኛ ሁላችንም በልደቱ ቀን ምን አይነት ተስፋ በልደቱ ቀን በመፈፀም ይህ ቀን/ዕለት/ የድኅነታችን መጀመሪያ በመሆኑ ከፍ ባለ አክብሮት ልናከብረው ይገባናል።

ይኸውም በመብል በመጠጥ በመደሰት ብቻ ሳይሆን እሱ የዓለም ፈጣሪ እኛን ለማዳን እንደድሀ በበረት መወለዱን መኳንንትን በክብር በጌትነት የሚያኈናፅፍ ዘላለማዊ አምላክ ሲሆን እንደ አንድ ተርታ ሰው በጨርቅ መጠቅለሉን የሁሉ መጠጊያ የሁሉ ረዳት የሁሉ ጥላ ከለላ ሲሆን ራሱን የሚያስጠጋበት አንዲት ጐጆ እንኳን አጥቶ በበረት ማደሩን እያሰብን አቤቱ ይህን ሁሉ ያደረግህ አምላካችንና መድኃኒታችን እኛን ለማዳን ከጠላታችን ከሰየጣን እጅ ነጻ ለማውጣትና ወደ ቀድሞ ክብራችን ለመመለስ ነው እያልን ከፍ ያለ ምስጋና ማቅረብ አለብን።

ስለዚህ የልደቱ ብርሀን እንዲያበራልን የጨለማውን ስራ ከእኛ አውጥተን እንጣል የጨለማውን መንገድ ትተን በብርሀን እንመላለስ። የዓለም መድኃኒት ክርስቶስ መወለዱን አውቀንና ተረድተን በንፁህ የተዘጋጀውን እጅ መንሻ ይዘን እንቅረብና ደስ እያልን እንስገድለት። የመወለዱን ዜና ላልተረዱ ወንድሞቻችን እንሆ መድኅን ክርስቶስ ለዓለም ቤዛ ለመሆን ተወልዶላችኋልና ወደ ልደቱ ብርሀን ቅረቡ እያልን እንናገር።

በልደቱ ሰውና እግዚአብሔር ሰውና መላዕክት ሕዝብን አህዛብን አስታርቆ በፍቅር አስማምቶ ለዓለም ሁሉ ሰላምን ስለመሠረተ ሰውና መላዕክት አንድ ሆነው ዓለምን ለማዳን ሰው የሆነውን አምላክ ለእግዚአብሔር በሰማያት ምስጋና ይገባል እያሉ አመሰገኑ፡፡

በደቂቀ አዳምም ዘንድ የሰው ፍቅር አገብሮት አምላክ ሰው ቢሆን ሰላም ሆነ፡፡እያሉ ሲያመሰግኑ አድረዋል፡፡ በዘመኑ ያሉ ሊቃውንት የሚያገለግሉበት መነፅር የራቀውን አቅርቦ የረቀቀውን አጉልቶ ከማሳየት በቀር በእጅ ሊያስጨብጥ እንደማይችል ቅዱሳን ነቢያትም ከ፭ሺህ ፭፻ ዘመን በኃላ ይፈጸም ዘንድ የነበረውን ተስፋ በራዕይ በተመስጦ እየተመለከቱ ምሳሌ ከመመሰል ፣ ትንቢት ከመናገር በቀር ከተስፋው የልደት ቀን ደርሰው በቅርብ የማየት ዕድል አላገኙም፡፡

የጌታችን መወለድ የሚሆንበት ዕለት በትውልድ የቆጠሩ እነ ሄኖክ በዕለት በሰንበት በሱባኤ የቆጠሩ እነ ኤርምያስ እነ ዳንኤል ከዕለቱ ደርሰው የልደቱን ብርሀን የቅርብ ተመልካች ሊሆኑ አለቻሉም፡፡ ሌሎችም እንሆ ድንግል በድንግልና ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች ብለው ትንቢት ይናገሩ የነበሩ እነ ኢሳይያስ ይልቁንም የልደቱን ነገርና የሚወለድበትን ልዩ ስፍራ አጉልቶ በመናገር የእግዚአብሄር ቦታውን የያቆብን ፈጣሪ ማደሪያውን እስኪገኝ ድረስ ለዓይኖቼ እንቅልፍን ፣ለቅንድቦቼም ሽልባትን፣ ለፊቶቸም ትሩፋትን አልሰጥም፡፡ እነሆ በኤፍራታ ሰማነው በጎል በበረት ተጥሎ አገኘነው፡፡ እንግዲያስ ለኛ ብሎ ከተወለደልን ወደ ቤተ እግዚአብሔር ወደ መንግስተ ሰማያት እንገባለን፡፡ መዝ ፩፻፴፪ ፣ ፬- ፯ እያሉ በግልፅ ያዩትን ትንቢት ሲናገሩ እነ ቅዱስ ዳዊትና እነ ሚኪያስ እንደ ዮሴፍና እንደ ሰሎሜ በልደቱ ጊዜ ተገኝተው የቅርብ ተመልካችና የደስታው ተካፋዮች ለመሆን አልተቻላቸውም፡፡

በተቀደሰ ልደቱ የገለፀውን የቸርነት ምስጢርን በዙርያው ያበራውን ብርሀን በቅርብ የተመለከቱ በመታደል የተመረጡ ዮሴፍና ሰሎሜ በቤተልሔም ዙርያ መንጋቸውን ተግተው ይጠብቁ የነበሩ የከብት እረኞች ናቸው፡፡

ከዚያም በኃላ ይህን ብርሀን ለማየት የታደሉ ሰብዓ ሰገል የምስራቅ ነገስታት ለአምላክነቱ ለንጉስነቱ የሚገባዉን እጅ መንሻ ይዘዉ በኮከብ እየተመሩ ከቤተልሔም ደርሰዉ የልደቱ በዓል ተካፋዮች ሆነዋል፡፡ ምንግዜም ቢሆን እግዚአብሔር ያረቀቀውን ምስጢር የተሠወረውን ነገር የሚገልፀው በሃይማኖትና በቅን ልቦና ለሚኖሩ፣ በመንፈሳቸዉ ንፁሐን ለሆኑ ደጋግ ሰዎች ነዉ፡፡ ነቢያት የእግዚአብሔርን ደገኛ ምስጢሩን ለማየት ይልቁንም ርእይዎ ነቢያት ለእግዚአብሔር ወተናፀሩ ገጸ በገጸ እሱ ባወቀ ነቢያት እግዚአብሔርን ፊት ለፊት አይተውታል ብሎ ሊቀሕርያቆስ እንደተናገረው ነቢያት የበቁት መንፈሳቸውን በማንፃት ነው፡፡

“ እኛም ዛሬ ቀድሞ የነበረ የሱን ነገር እንነግራችኃለን በጆሮአችን የሰማነው በዐይናችን ያየነው ስለህይወት ነገር በእጃችን ዳሰን የተናገረነው እሱ ነው፡፡ ብሎ ሐዋርያው ዩሐንስ እንደተናገረው / እንዳስተማረው/ እናንተም ከእኛ ጋር ትተባበሩ ዘንድ እንነግራችኃለን፡፡ አንድነታችንም ከአብ ከባህርይ ልጅም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋራ ነው፡፡ ደስታችሁም በእኛ የተፈፀመች ትሆን ዘንድ እግዚአብሔር ብርሀን እንደሆነ ምንም ጨለማ እንደሌለበት እንነግራችኃለን፡፡

እንግዲህ የልደቱ ብርሀን ለዓለም ሁሉ ስለሆነ የዓለም ቤዛ የሰው ሁሉ መድኃኒት ዛሬ ተወለደ እያልን ሁላችንም በአንድ ቃል ልናመሰግነው ይገባናል፡፡

እርሱ የባህሪይ አምላክ የባህሪይ ገዥ ሲሆን ራሱን ዝቅ አድርጎ ስለሰው ፍቅር መስዋዕት በመሆን በጨለማ ለነበሩት እንዳበራላቸው በሲኦል የተጋዙትን ነፃ እንዳወጣቸው የዓለም መሪዎችና ታላላቅ ነገስታት ሁሉ የመድኃኒታችን አሠረ ጽድቅ ተከትለው ስለዓለም ሰላም እንዲጥሩ ለሰው ልጅ ሁሉ ትክክለኛ መብት ሰላም ፍትህ እንዲኖራቸው አጥብቀን እንጸልያለን፡፡

በዓሉን የሰላምና የእውነት በዓል ያድርግልን፡፡

ምንጭ፣ አስተረዓየ ዘኢያስተርኢ

በመንበረ ፓትሪያርክ የተዘጋጀ